የሰ/መ/ቁ.29269

ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አቶ ሳሙኤል ገዛኸኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ ዋለልኝ አያሌው ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ለመች ላቀው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት 2ኛ ተጠሪ ባለዕዳ ሆነው በምዕ/ጉጃ መስተዳደር ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ. 8291 በሆነው መዝገብ ላይ የአፈፃፀም ክሱ እየታየ ባለበት ጊዜ የአሁኑ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.418 ን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውም ምክንያት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የባለዕዳዋን ንብረት አስቀድሜ ያስከበርኩት ስለሆነ ቤቱን ባለመብቱ አንዲረከብና ስመ ንብረትነቱም እንዲዛወርለት የተሰጠው ትዕዛዝ ቀሪ አንዲሆንልን ይታዘዝልን የሚል ነው፡፡ በማስረጃነትም በዚሁ ንብረት ላይ የማስከበሪያ ትዕዛዝ ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ያሰጠበት መሆኑንና ባለዕዳ በተባለችው በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ በዋስትና



ግዴታ ምክንያት ክሶ ፍርድ ያሰጠበት መሆኑን የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

በዚሁ አቤቱታ ላይ መልስ የተሰጠበት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ከገለፀ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ምንም እንኳን የአሁን አመልካች በዚሁ ንብረት ላይ የማስከበሪያ ትዕዛዝ ያሰጠበት መሆኑ ቢረጋገጥም ማስከበር ብቻውን የቀዳሚነትን መብት የሚያስጥ ሆኖ አላገኘነውም ስለሆነም የቀረበው የአፈፃፀም ክስ ይቋረጥልኝ አቤቱታ ውድቅ ነው በማለት በይኗል፡፡

በዚህም ብይን የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሳው አከራካሪ ነጥብ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ወገን ማን ነው? የሚለው መሆኑን ለይቶ በጭብጥነት ከያዘ በኋላ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2ኛ ተጠሪ ላይ አስቀድሞ ክስ ያቀረበ እና አስወስኖ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበ መሆኑ ቢረጋገጥም 1ኛ ተጠሪ አቶ ዋለልኝ አያሌው ለ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ብር 80,000.00/ሰማንያ ሺህ/ ብድር ሲሰጡ ይህ የብድር ገንዘብ በተባለው ጊዜ ውስጥ ባይመለስ የክርክሩ መንስኤ የሆነውን ቤት ለማስረከብ የውል ግዴታ የገቡ መሆናቸውንና እንደ ግዴታቸው የገንዘብ መክፈያ ጊዜው የብድሩን ገንዘብ መመለስ አለመቻላቸው ተረጋግጦ በሥር ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይኸው በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በቁጥር መ/1/1984 ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት እንዲረከቡ ተወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበውም ከዚሁ ንብረቱን ይረከብ የሚለው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመሆኑ እና ንግድ ባንክ በቀጥታ ክሱ ጊዜ ይኸው ንብረት ታግዶ እንዲቆይ ማስደረጉም የፍርድ ባለመብት በቤቱ ላይ ያገኘውን መብት የሚያሳጣ ሆኖ ባለመገኘቱ የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት

ያለው አይደለም። እንዲሁም አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ተከብሮ የመያዙ እውነታም ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በባለሀብቱ ላይ ያስፈረደ ወገን በቀረበ ጊዜ የተያዘውን ንብረት ለመውሰድ እንደማይከለክል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ፍ/ቁ.403 ይደነግጋል። አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን በመያዣ የያዘው ባለመሆኑም ቀድሞ ክስ ማቅረቡ ብቻውን የ1ኛ ተጠሪን የአቶ ዋለልኝ አያሌውን መብት የሚያስቀር አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመንተራስ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል። የአመልካችም የሰበር አቤቱታ ፍሬ ቃል፡-

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው የሰጠው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.403 የተመለከተውን ድንጋጌ ትክክለኛ ትርጉም የተከተለ አይደለም።

ከ1ኛ ተጠሪ ይልቅ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ቀድመን መብታችንን ያስጠበቅን መሆኑ እየታወቀ እና በዚህም የተነሣ በሥነ ሥርአት ህጉ የተሰጠን ዋስትና እያለ ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል።

ይህም እንኳ ቢታለፍ የፍርድ ባለመብት እንደመሆናችን መጠን የባለዕዳዋ ንብረት ተሸጦ እንደየድርሻችን መከፋፈል ሲገባን ለ1ኛ ተጠሪ ብቻ እንዲሰጥ መደረጉ የህግ ድጋፍ ያለው ባለመሆኑ ይኸው ይታረምልን የሚል ነው።

ተጠሪዎችም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት ህግን መሠረት ያደረገ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

እኛም ጉዳዩን መርምረናል። እንደመረመርነውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የብድር ውልን መሠረት አድርጎ ክስ ከማቅረቡ እና ከማስወሰኑ በፊት የአሁን አመልካች በ2ኛዋ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ምክንያት ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ይኸው ክርክር ያስነሳው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ያሳገደው ለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል



የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም። ይህም መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች በኩል የተፈፀመው ተግባር በ2ኛ ተጠሪ ላይ የገንዘብ ክስ አቅርቤአለሁ፤ እንደ ክሱ ባስፈርድ ፍርዱ ውጤት ያገኝ ዘንድ የተከሳሽ ንብረት ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማለት ተከብሮ ይቆይልኝ የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3044 እንደተመለከተው ይህ የማሳገድ ተግባር ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት መሆኑን ያመለክታል። ይኸውም ፍርድ ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ለማረጋገጥ አንዱ ወገን ለሌላው ወገን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሚያሰጠው የማስከበሪያ ትዕዛዝ አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.154 መሠረት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ ከፍርድ በፊት በንብረት ላይ የሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ ነው። ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በዚሁ መሠረት የ2ኛዋ ተጠሪ ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ተከብሮ እንዲቆይ ያስደረገ ለመሆኑ የተለየ ሆኖ ካልተገኘ አመልካች በዚሁ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያገኘ መሆኑን አረጋጋጭ ነው። እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትንተና የመያዣ መብት ሁልጊዜ ከውል ብቻ እንደሚመነጭ ተደርጎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 እንደተደነገገው መያዣ ከውል ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ ወይም በፍርድ ሊቋቋም ይችላል። በዚህ መሠረት አመልካች ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመነጨ የመያዣ ውል ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ገንዘብ ጠያቂ ያስያዘው እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠየቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት ለእርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3059/1/ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የጠየቀው ዳኝነት ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ህግ ከሚደነግገው ውጭ በሥር ፍ/ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል።

አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተከብሮ የመያዙ እውነታ ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በንብረቱ ባለሀብት ላይ ያስፈረዱ

ወገኖች በቀረቡ ጊዜ የተያዘውን ሀብት ከመውሰድ እንደማያግዳቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 403 ተደንግጓል በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትንታኔም ተመልክተናል፡፡ በመሠረቱ የዚህ ድንጋጌ አግባብነት ከድንጋጌው ርዕስ እንደምንመለከተው የአንድ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ይኸው ንብረቱ በእነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል የሚደነግግ እንጂ እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አባባል አንደኛው ገንዘብ ጠያቂ ብቻውን ጠቅልሎ እንዲወስድ የሚያስችል አይደለም፡፡ የድንጋጌውም ተፈፃሚነት የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት በተራ ባለገንዘቦች መካከል ማከፋፈል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የተወሰነ እንጂ የቀዳሚ መብትነት የሚመለከት አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ከፍርድ የመነጨ የመያዣ ውል የመኖሩን እውነታ ወደ ጐን በመተው ንብረቱን በሚመለከት በንብረቱ ላይ ያስወሰነው 1ኛ ተጠሪ ነው የሚለውን ብቻ መሠረት በማድረግ ለዚሁ 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት እንዲኖረው በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የምዕ/ጐጃ መስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈ/መ/ቁ.8291 በመስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የአማራ ብሔ/ክል/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው በመሆኑ ይኸው በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የሆቴል ቤት ድርጅት ተሽጦ ከሽያጩ ገንዘብ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚፈልገው ዕዳ በቅድሚያ



ሊውል ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በዚሁ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈፅም አዘናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ